# “ዛሬ እናንተ ይህን ሰንሰለት ሰብራችሁታል”- ገብሩ አስራት

ታህሳስ 4/04/2002ዓ/ም በማይጨው ከተማ አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉኣላዊነት ፓርቲ አንድ ትልቅ ህዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ ነበር።

በዚህ ስብሰባ ውስጥ የፓርቲው ሊቀ መንበር አቶ ገብሩ አስራት ስለወቅታዊ ሁኔታ፣ስለ ረሃብ፣ ኢኮኖሚ ፣ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ችግሮች በበለጠ ደግሞ አረና ትግራይ ከመድረክ ጋር ሆኖ ስለሚያካሂደው እንቅስቃሴ፣ መድረክ ከስነምግባር ኮድ ለምን ረግጦ እንደወጣ በአባላቶቹ ላይ ስለሚደርሰው በደልና አረና ትግራይ የሚከተለው /አይዶሎጂ/ ፅንሰ ሃሳብ ከኤርትራ ጋር ስላለው ሁኔታ ወዘተ. በእለቱ በሊቀ መንበሩ ሪፖርት ቀርቧል። አቶ ገብሩ ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ከህዝቡ አስተያየትና ጥያቄ ካለ በማለት ጠይቀው ብዙ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበዋል።

ከጥያቄዎቹ መካከል አረና ትግራይ ከህወሐት በምን ይለያል? ከነብርሃኑ ነጋ ጋር በምን ትለያላችሁ? ከቅንጅት ጋር ለምን ተሰለፋችሁ? አረና ካሸነፈስ ምን ለማድረግ አስቧል? የመገንጠል መብት እንዴት ታዩታላችሁ? አረና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የነበረው ውይይት ለምን ረግጦ ወጣ? ከመንግስት ካድሬዎች በደል እየደረሰብን ነው? ቢፒአር እየተባለ ሰው እየተንሳቀለ ነው። የትምህርት ፖሊሲ እየተበላሸ ነው ያለው፤ ይህንን ለማሻሻል ምን ታስቧል? ወደብ አስፈላጊ ነው ግን ማምጣት ይቻላል ወይ? ወደዚህ ስብሰባ ሰው እንዳይገባና እንዳይሳተፍ በር ላይ ሆነው የሚከለክሉ ሰዎች አሉ እና ይሄንን እንዴት ማስወገድ ይቻላል? አብዛኞቹ ጥያቄዎች ከመንግስት አካላት የሚደርሰው በደሎች ሁሉ ዘርዝረው ተናግረዋል በግልም ለአቶ ገብሩ አስራት አንተ ለምን ከህወሓት ለምን ለቀቅክ? ለምን ይቅርታ አልክ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ።

ይህ በንዲህ እንዳለም አንድ አንድ አስተያየቶችም ተሰጥተዋል በትግራይ በ18ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ ተቃዋሚ ፓርቲ በማግኘታችን በጣም እድለኞች ነን፤ ተቃዋሚ ፓርቲ ማለት የአንድ ህዝብ ችግር እንዲወገድ የሚያደርግ ነው፤ ኢሃዲግ አባል ቢያበዛው ትርጉም የለውም፤ በዚህ ስብሰባ ውስጥ ብዙ ሰላዮች አሉን፤ ከገብሩ ጋር በመገናኘታችን እድለኞች ነን፤ ከትግራይ ህዝብ ጠላቶች ጋር የተሳሰረው ኢሃዴግ ነው፤ ብዙ አልመጣም ብላችሁ ተስፋ አትቁረጡ በርቱ ከጎናችሁ ነን። የሚሉ አስተያየቶች ከተሰብሳቢው ተንፀባርቋል አቶ ገብሩና አቶ ብርሃኑ በርሀ የድርጅቱ ምክትል ሊቀ መንበር በየተራ በመሆን እንዲህ በማለት መልሰዋል። ‘’አረና ከህወሓት የሚለይበት ዋናው በአይዶሎጂ ነው። ኢሃዲግ የሚከተለው አብዮታዊ ዲሞክራሲ መሆኑ አስተሳሰብ ጨቋኝ፣ ከፋፋይ፣ ወጋኝና ኢ-ዲሞክራሲያዊ መሆኑ። አረና የሚከተለው ግን ሊበራል ዲሞክራሲ ነው’’ በማለት ገልፀዋል።

ከነ ብርሃኑ ነጋ በምን ትለያለችሁ ለሚለው ደግሞ አቶ ብርሃኑ ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል ‘’አረና ህጋዊ ፓርቲ ነው። በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገዶች ነው የሚታገለው። የነብርሃኑ ነጋ ግን ሰላማዊ ትግል በኢትዮጵያ እንደማያዋጣና ብረታዊ ትግል እንደሚያስፈልግ ነው የሚገልፀው’’ ብለዋል።

ከቅንጅት ጋር ለምን ተሰለፋችሁና? ለምን ይቅርታ አልክ? ለተባለው ጥያቄ ደግሞ ‘’እኛ ከቅንጅት ጋር አልተሰለፍንም አንሰለፍምም እኛ የተሰለፍነው ከ8 ፓርቲዎች ጋር ነው። አንድነትም ከምርጫ 97ዓ/ም ቧሃላ የተመሰረተ ፓርቲ ነው። ስለዚህ ከቅንጅት ጋር የተሰለፉ ኢሃደግ ናቸው። የቅንጅት መስራቾችና ዋና አከራሪዎች አቶ ሃይሉ ሻውልና አቶ ልደቱ አያሌው ናቸው። እነዚህ ደግሞ ከገዢው ፓርቲ ኢሃዴግ ጋር ሆነው ነው የሚሰሩ ያሉት። ልደቱ ‘የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የበለጠ ገንዘብ /በጀት/ ያገኛል። ትእምት መወረስ አለበት’ እያለ የሚናገር የነበረው ልደቱ ነው። ሃይሉ ሻውልም ‘የተከለሃይማኖት ሰፈር ነዋሪዎች ሳይቀሩ መርጠውናል’ እያለ የትግራይ ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ እንዲነጠል የሚያደርግ የነበረ ሰው ነው። ስለዚህ ከትግራይ ህዝብ ጠላት ጋር ያበረው ኢሃዲግ ነው። ብለዋል አቶ ገብሩ አስራት። አያይዘውም ‘’እኔ ይቅርታ ያልኩት በ1997 ዓ/ም እነ መለስ ባድመ ለኤርትራ ለመስጠትና የሄጉ ውሳኔ በመርህ ደረጃ ከተቀበለው ቧሃላ ነው። ምክንያቱም በባድመ ላይ ብዙ ሂወትና ንብረት ወድመዋል። ስለዚህ ይህንን ሽፋፍነው ሊያልፉ ስለፈለጉ ነው የተቃወምኩት። ሌላም የኤርትራ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ የባህር ወደብ እየተገባት በማጣትዋ ትልቅ ስህተት ተሰርቷል ብየ ይቅርታ ብያለሁ እንጂ ባካሄድኩት ትግል ምንም ታክል አይቆጨኝም። አሁንም በኢትዮጵያ ሉኣላዊነት የሚነሳ ጉዳይ እቃወማለሁ’’ በማለት በመናገራቸው ከተሰብሳቢዎቹ ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተደርጎላቸዋል።

የመገንጠል መብት እንዴት ታዩታላችሁ? ለሚለው ጥያቄ አቶ ብርሃኑ ሲገልፁ ''ለኢትዮጵያ ህዝብ ወሳኝ ነገሩ አንድነቱ ነው። መገንጠል መብት አይደለም ግን ችግር ካለ የማንኛውም ዜጋ ውሳኔ ያስፈልጋል ክልሎች ብሔር ብሔረሰቦች ራሳቸው ለራሳቸው ካስተዳደሩ ኢኮኖሚያቸው ካሳደጉ ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ከተከበረላቸው መገንጠል የሚፈልግ አይኖርም። ስለዚህ ለኢትዮጵያ መገንጠል፣ መጋጨት፣ መቀናናት በምንም ተአምር አይጠቅማትም።''

ዓረና ካሸነፈ ምን ለማድረግ አስቧል? ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ ማንኛው ዜጋ እኩል መሆኑን ማረጋገጥ፤ ሞያ መከበር እንዳለበት፤ የትምህር ፖሊሲውን መቀየር፤ በትምህርትና ስራ ልምድ የሚበልጥ ሰው ደረጃውን ማግኘት የኢኮኖሚ ነፃነት መስጠት ከደህንነትና ከፀጥታ ሃይሎች መንግስ እጁን የሚያወጣ መሆኑን፤ ለኢትዮጵያ አንድነት መታገል ከሁሉም የበለጠ ሰው በነፃነት እንዲያስብና እንዲሰራ እንታገላለን'' ወዘተ ብለዋል።

ግፍ እየደረሰብን ነው እንዴት መከላከል ይቻላል? ለሚለው ደግሞ ይህንን የምንከላከለው ህዝብ ይዘን ነው ህዝቡ ሃይል አለው ብዙ ችግሮች መስዋእት ሊያጋጥም ይችላል። ይህንን ካላደረግን ደግሞ ሞተናል ማለት ነው መድፈር አለብን። ማንዴላ 27 አመት ሲታሰር ሲፈታ ያለፈ ታጋይ ነው። እናንተም ልትታሰሩና ልትንገላቱ ትችላላችሁ ብዙ ችግሮችና ፈተናዎች ያጋጥሚችኋል። አሁን ለምሳሌ እኔ በኢትዮጵያ ልሰራ አልችልም ምክንያቱም ለኔ ያሰሩኝ ሰዎች ወይ ደግሞ ድርጅቶች ግብር ይጨመርበታል ያስፈራሩዋቸዋል ይህ ግን ከፖለቲካ ሊያርቀኝ አይችልም። ከሁሉም በነፃነት ማሰብ አለባቸሁ በማለት አቶ ገብሩ ተናግረዋል።

በስተመጨረሻ የፓርቲው ሊቀ መንበር አቶ ገብሩ አስራት ለተሰብሳቢዎቹ ምክር አዘል አስተያየቶች ሰጥተዋቸዋል። ''አሁን እዚህ ያላችሁ ወጣቶች ዛሬ ይህንን ሰንሰለት ሰብራችሁ ገብታችኋል ቀጥሉበት። ግፍ ግርፊያ መድልዎ መገለል ይደርስብናል ግን እናሸንፋለን አላማ ካለ የማይሸነፍ ነገር የለም። ደርግ፣ መሶሎኒ፣ ሂትለር፣ ወድቀዋል የማይ ወድቅ የለም። ነፃነታችሁን አስፉት ለአገር ለውጥ የሚያመጣ ነፃነት ነው ብለዋል።

እኔም የአረና ፓርቲ ሊቀ መንበር አቶ ገብሩ ስብሰባውን ከጨረሱ በኋላ ስለእለቱ የነበረው ሁኔታ በሚከተለው መልኩ አነጋግሬያቸዋለሁ።

ጥያቄ፡- ጠቅለል አድርገው ስለስብሰባው ሁኔታ ቢገልፁልኝ

አቶ ገብሩ፡- የህዝቡ ስሜት እንደማንኛውም ህዝብ ለውጥ ፈላጊ ነው። አማራጭ ነፃነት እንዲኖረው ጭቆና እንዲወገድ ይፈልጋል። ገዢው ፓርቲ ግን ህዝቡ እንዳያተነፍስና፣ እንዳይንቀሳቀስ፣ አማራጭ እንዳያይ፣ እንዳይደራጅ ባለው አቅም እየተጠቀመ ነው። እነዚህን ወንጀሎች የሚፈፅሙት ደግሞ የመንግስት አካላት፣ የፀጥታ አካላት፣ በኢኮኖሚው መስክ እየተንቀሳቀሱ ነው። በመንግስት አካላት ማለት የተደራጁ ፓርቲዎች ተቆጣጥረው ነፃ መንፈስ /አስተሳሰብ/ ካለ በአስተዳደሩ ይቀጣዋል።

የፀጥታ አካሎች ደህንነት ፖሊስ ሰዎች እንዳይተነፍሱ እያደረጉዋቸው ነው። እኛ ስብሰባ አለን ለማለት ለህዝቡ በማይክራፎን አድርገን በከተማው በመኪና ለመዞር ያደረግነው ሙከራ በ5ኛው ግዜ ነው የተሳካልን። ለባለ ንብረቶቹ የደህንነት አካላት ስልክ እየደወሉ በማስፈራራት ስራችንን አስተጓጉለዋል 5 ግዜ ነው መኪና የቀየርነው። ይህም አይበቃቸው ብሎ እኛ በዞርንበት ከኋላችን በመሆን 'ነገ አስቸኳይ ስብሰባ አለ ያልተገኘ ቅጣት ይቀጣል እያሉ እየረበሹ ነው የዋሉት።

በስብሰባው ዕለትም የከተማው ከፍተኛ አመራሮችና አስተዳዳሪው ሳይቀር በስብሰባ አዳራሽ ደጃፍ ላይ በመሆን ህዝቡ ወደ አዳራሹ እንዳይገባና እንዳያዳምጥ ሲከለክሉት ነው የዋሉት። የካሜራ ባለሞያዎችም ወደ አዳራሹ እንዳይገቡና እንዳይቀርፁ በደህንነት አካላት ማስፈራራት ስለደረሰባቸው ሊገቡ አልቻሉም።

በኢኮኖሚው መስክ በጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የሴፍቲ ኔት ስራዎች የኢሃዲግ አባሎች ካልሆኑ በስተቀር ወደ ስራው ሊገባ አይችልም። ስለዚህ ገዢው ፓርቲ በህዝቡ ላይ ትልቅ ጫና እየፈጠረበት ነው ያለው። የማይጨው ስብሰባ በዚህ ትልቅ ውስብስብ ሁኔታ እያለ ህዝቡ አዳራሹ ውስጥ መገኘቱ ነው ያስደነቀኝ። በጣም ከባድ የሆነ ጫና ካለው ሁኔታ በጥሶ ችግሩን ሊቀርፍ የሚችል ሰው እንደጠበቅነው ሆኖ አላገኘነውም። ግን ያቀድነው ስብሰባ በሰላም አካሂደናል። ገዢው ፓርቲ ፈልጎ የነበረው በአዳራሹ ማንም ሰው እንዳይገኝ ነው ይህንን ለማስፈፀም ደግሞ የመንግስት ሰራተኞች፣ አስተማሪዎች በየመስራቤቱ

ሃይለኛ ስብሰባ አለ እየተባለ መለጠፍ ነው። የከተማው ነዋሪ፣ የገጠሩ ነዋሪ ደግሞ የምርጫ ታዛቢዎች ምርጫ አለ እየተባለ ነው ስብሰባውን ለማጨናገፍ የተሞከረው።

መንግስት ሰራተኛው ስብሰባውን ጥሎ ህዝቡም አፈናውን ሰብሮ ነው ወደ ስብሰባ አዳራሽ የገባው። ተሰብሳቢው ጨዋነት በተሞላው አኳኋን ነው ጥያቄዎች እየጠየቀ፣ መሰረታዊ የሆነ ልዩነትና መረጃ ለማግኘት የፈለገው።

አብዛኛው ህዝብ ከአዳራሹ ውጪ በማይክራፎን የሚተላለፈውን መልእክት ደጅ በመሆን ሲከታተል ነው የዋለው። እንዳይገባ የፀጥታ ሃይሎችና ካድሬዎች አዳራሹ ደጃፍ ስለቆሙ ነው። ባጠቃላይ በህዝቡ ትልቅ ለውጥ ነው ያለው የፍርሃቱን መጋረጃ እንደቀደደ ነው የማየው።

የዚህ ሁሉ ችግር ፈጣሪዎች የአፈናውን መርበብ መሪዎች የህወሓት ካድሬዎችና የፀጥታ ሃይሎች ናቸው። የካድሬዎቹ ዋና መመዘኛ ለተቃዋሚዎች ስር መሰረቱን ማጥፋት ነው እንጂ ዲሞክራሲ፣ ፍትህ፣ ልማት አይደለም። ይህ የሆነው ደግሞ የገዢው ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች የካድሬዎቹን መመዘኛ በማውጣታቸው ነው። ይህ የሚሆነው ገዢው ፓርቲ ለ20ና 30 ዓመት በስልጣል ለመቆየት የሚወስደው እርምጃ ነው።

ጥያቄ፡- የህዝቡ ዋናው መሰረታዊው ስሜቱና ጥያቄው ምንድነው

አቶ ገብሩ፡- ሁሉም ህዝብ ፍርሃት አላስወገደም። ስሜቱ ግን አንድ ነው። ብዙ ማህበረሰቦች ማለት ነጋዴዎች፣ መንግስት ሰራተኞች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች በተናጠል አጊንተናቸው ነበር ለውጥ ይፈልጋሉ። ግን ሊቃወሙ አይችሉም ምክንያቱም ነጋዴው ግብር ይጨመርበታል፣ ሰራተኛው የትምህርት ይሁን የደሞዝ እድገቱ ወይም የስራ እድገት ከተቃወመ የለውም። ገበሬዎችም ከሴፍቲኔት ተጠቃሚነት ይባረራሉ አሁንም ለምሳሌ በደቡባዊ ዞን ለማይጨው ከተማ የአረና ከፍተኛ አመራር የሆነ አቶ አድሃና ንጉሰ የተባለ አባል ቤተሰቦቹ ከሴፍቲኔት አባል ተባረዋል። የአረና አባሎችም በደል እየደረሰባቸው ነው በጣም ፍርሃት አለ።

በስብሰባው አብዛኛው የመጣው ፍርሃት ያለው ነው። ተማሪው አስተማሪዎቹ ማርክ እንዳይቀንሱበትና እንዳያባረሩ የሰጉ ናቸው። የፓርቲው አላማውና አማራጭ በማግኘታችን በጣም ጠቃሚ ነው። ግን አፈናውን እንዴት ብለን ማስወገድ አለብን? መፍራት እንደሌለብን አማራጭ አስፈላጊ መሆኑ የሚሉ ብዙ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የሚጠይቁና እርምጃ መወሰድ እንዳለበት የሚጠቁሙ ናቸው። ስለዚህ እኔ በስብሰባው የተሰበሰበው ህዝብ ስሜቱ እንደዚህ ነው የማየው።

ጥያቄ፡- በቀጣይ አረና ምን ለማድረግ ነው ያሰበው?

አቶ ገብሩ፡- እኛ በመጀመርያ ግዜ በመቀሌ አንድ የአረና ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ አካሂደናል ከመቀሌ ውጭም ደግሞ ሁለተኛ ስብሰባ በማይጨው አካሂደናል ይህ ማለት አረና ከመቀሌ አልፎ በየወረዳዎቹና ዞኖች ፍርሃትን ለማስወገድ እየተንቀሳቀሰ ነው እስከ ምርጫ የሚጠናቀቅ በመላው ትግራይ ብዙ ስብሰባዎች እናካሂዳለን። ብዙ መሰናክሎች ቢኖሩም እነዚህን ለማስወገድ እንጥራለን።

ታደሰ ተስፋይ

0914036327